ምስጋና

ይህ የሥርዓተ ጾታ ክበብ የአደረጃጀት፣ አመራር እና አሰራር ስርዓት *መመሪያ* ለመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት እንዲሰጥ የተዘጋጀ ነዉ።

በዚህ የዝግጅት ሂደት ዩኒሴፍ-ኢትዮጵያ የትምህርት ክፍል የቴክኒክ እና የፋይናንስ ድጋፍ እንዲሁም የአለም ባንክ የዝግጅት ሂደቱን በማስተባበር በኩል ላደረጋችሁልን ድጋፍ የላቀ ምስጋናችን ይድረሳችሁ ።

በተጨማሪም *መመሪያዉ* ለማዘጋጀት በተካሄዱ የቪድዮ-ኮንፍረንስ፤ ወርክ-ሾፕ እና የምክክር ስብሰባዎች በመገኘት ግብዓት በመስጠት ለተሳተፋችሁ ባለድርሻዎች እና የልማት አጋሮች ምስጋና እናቀርባለን።

ትምህርት ሚኒስቴር

አዲስ አበባ

2012 ዓ.ም

ይዘት **ገጽ**

ምስጋና

ስለ መመሪያው ማብራሪያ

ክፍል-አንድ፤መግቢያ፤ በትምህርት ቤት የሚቋቋም የስርዓተ ጾታ ክበብ

1.1. የጾታ እና ሥርዓተ-ጾታ ፅንሰ ሃሳብ

1.2. ሥርዓተ-ጾታ እና ትምህርት: - የተገላቢጦሽ ተፅዕኖ

1.3. የሥርዓተ-ጾታ ክበብ ጠቀሜታ

ክፍል-ሁለት፡የስርዓተ ጾታ ክበብ ነባራዊ ሁኔታ ትንተና

2.1 የሥርዓተ-ጾታ ክበብ፡ በኢትዮጵያ-

2.2.በመመሪያዉ ዉስጥ ለሥርዓተ-ጾታ ክበብ የተሰጠ ትርጉም

2.3.ሥርዓተ-ጾታ ክለብ አላማዎች

2.4.የሥርዓተ-ጾታ ክለብ መርሀዎች

ክፍል-ሶስት፤የሥርዓተ ጾታ ክበብ አደረጃጀት፤አመራር እና አሰራር

3.1. አባልነት

3.1.1. ምዝገባ

3.2.አደረጃጀት

3.2.1..የስርዓተ ጾታ ክለብ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት

3.3. አመራር

3.1.1. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተግባር እና ሃላፊነት

3.3.2.የስብሰባ ጊዜ የጠቅላላ ጉባዔ

3.4. በሥርዓተ ፆታ ክበብ የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት

3.4.1.የህፃወት ክህሎት ስልጠና መስጠት

3.4.2.በጾታ እኩልነት ላይ የህብረተሰብ ንቅናቄ ስራዎችን ማካሄድ

3.4.3.የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ ላይ ትምህርት እና አገልግሎት መስጠት

3.4.4.የጾታዊ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ ተማሪዎችን መለስተኛ የምክር አገልግሎት መስጠት

3.4.5.ከባለድርሻዎች እና የልማት አጋሮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር መንቀሳቀስ

3.4.5.1.የዉስጥ ባለድርሻዎች

3.4.5.2.የዉጭ ባለድርሻዎች

3.4.6.የሴት እና የወንድ ተማሪዎች እኩል ተጠቃሚነት ላይ ምርምር እና ጥናት ማካሄድ

ክፍል-አራት፡ክትትል፤ድጋፍ እና ግምገማ

4.1 በሥርዓተ ጾታ ክበብ ክትትል እና ድጋፍ ስራ የሚሳተፉ አካላት

4.2 ሥርዓተ ጾታ ክበብ ተግባራት የክትትል፣ ድጋፍ እና ግምገማ ርዕሰ ጉዳዮች

4.3 የስርዓተ ጾታ ክበብ የዉጤት ደረጃዎች፤ሂደት፤አመልካች እና ሥልቶች

4.4 የስርዓተ ጾታ ክበብ መረጃን ማጠናቀር

ስለ መመሪያው ማብራሪያ

ይህ መመሪያ በመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተቋቋመዉን "የሥርዓተ ጾታ ክበብ" ለማጠናከር እንዲሁም አዲስ ለሚቋቋምበት የሥራ መመሪያ አድርገዉ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ የተዘጋጀ ነው። በሀገራችን በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በክፍል ዉስጥ የሚካሄደዉን የመማር ማስተማር ተግባር ለመደገፍ የተለያዩ ክበባት በማቋቋም እንዲንቀሳቀሱ የሚደረግ ሲሆን የዚህ መመሪያ ዋና ትኩረት ግን በትምህር ቤት ደረጃ የጾታ እኩልነት የማስፈን ስራን በተጓዳኝነት ለማከናወን ስለሚቋቋመው የሥርዓተ ጾታ ክበብ አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማዎች ፤እንዴት ማደራጀት፤ መምራት እና ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባት እንዳለበት የሚያመለክት ሰነድ ነው።



በዚህ መሰረት በሀገራችን በሚገኙ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጾታ እኩልነት ማስፈን የሚለዉን ዓላማ ይዘዉ የተቋቋሙ ክበባት የተበታተነ አደረጃጀት ያላቸዉ ስለሆነ ይህን አካሄድ በአንድ መዋቅር ሥር ማምጣት ፤ሥራቸዉን ወጥነት ባለውና በተጠናከረ ሁኔታ መፈፀም እንዲቻል ጉልህ ሚና ይኖረዋል። ለምሳሌ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የጾታ እኩልነትን ማስፈን የሚል አላማን ያነገቡ "የልጃገረዶች ክበብ" ፣ "የልጃገረዶች መድረክ" "የሴቶች ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ" አልፎ አልፎም "የስርዓተ ጾታ ክበብ" በሚል ስያሜ ተደራጅተው እንዲቀሳቀሱ ይደረግ የነበረዉን አካሄድን ወደ አንድ በማምጣት "የሥርዓተ ጾታ ክበብ" የሚል ስያሜ በመያዝ ብቻ ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነዉ።

ትምህርት ሚኒስቴር በ 1989 ያዘጋጀዉ የተጓዳኝ ክበባት አፈፃፀም መመሪያ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚማሩትን ትምህርት በተጓዳኝ ክበባት በኩል መረጃ እንዲለዋወጡ ፣ ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ እና ተሳትፏቸውን እንዲያጎለብቱ የሚረዳ መሆኑን በማመልከት ትምህርት ቤቶች ክበባትን ማቋቋም ያለባቸው መሆኑን ያመለክታል።በዚህ መሰረት ይህ የሥርዓተ ጾታ መመሪያ የተዘጋጀው የትምህርት ሚኒስቴር ያወጣዉን የተጓዳኝ ክበባት አፈጻጸም መመሪያን መሰረት በማድረግ ነዉ።

በየትምህርት ቤት የተቋቋሙ የሥርዓተ ጾታ ክበብ አጠቃላይ እንቅስቃሴ እንዴት መሆን እንዳለበት ለማሳየት የትምህርት ቤቱ አመራሮች ይህን ሰነድ የተግባር መመሪያ አድርገው መጠቀም የሚገባቸዉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መመሪያዉ የክበብን ዓላማ እና ስኬቶች ከሥርዓተ ጾታ ጉዳዮች አንጻር በመቃኘት እንዲያካትት ተደርጓል።

ይህ መመሪያ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላትን በማነቃነቅ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እንዴት ድጋፍ ማስባሰብ እንደሚቻል በዝርዝር ከማብራራቱ በተጨማሪ በትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ውጪ በጾታ እኩልነት ላይ ጽኑ አቋም ያሏቸውን ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እንደ ተምሳሌት በመውሰድ ትምህርት ቤት ድረስ በመምጣት ልምዳቸዉን በማካፈል የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ የሚያመለክቱ አቅጣጫዎችን የተቀመጡ ሲሆን ተማሪዎች ከእነዚህ በተምሳሌትነት ከሚጠቀሱ የህብረተሰብ አባላት ያገኙት ተሞክሮ መሰረት በማድረግ በሥርዓተ-ጾታ ክበብ በንቃት የሚሳተፉበት ዕድል ይኖራል ከሚለዉ ግምት በመነሳት የሚሰራ መሆኑ ተመልክቷል።

በመጨረሻም በዚህ መመሪያ ውስጥ በተቀመጠዉ የክበቡ አደረጃጀት መሰረት ፍቃደኛ የሆኑ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ (ሴትና ወንድ ተማሪዎች፤መምህራን እና የአስተዳደር ሰራተኞች) አባል በመሆን የሚሳተፉ መሆናቸዉን ከማሳወቅ በተጨማሪ ተሳትፎቸዉ በምን መልኩ መገለጽ እንዳለበት ተቀምጧል።

ከዚህ በተጨማሪ መመሪያዉ በትምህርት ቤት የሚገኙ ፣ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች መብታቸውን ከማረጋገጥ አኳያ የሚጠቀሱ መርሆዎችን የያዘ ከመሆኑም ሌላ የክበቡን እንቅስቃሴ ለማጠናከር የክትትል እና ግምገማ ስራዎች ምን መሆን እንዳለባቸው እንዲሁም የሚጠበቁ ውጤቶችና አመልካቾች እንዲሁም የክበቡ መረጃ የማጠናቀር ተግባር በመመሪያው ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል።

ክፍል አንድ ፡

መግቢያ ፡በትምህርት ቤት የሚቋቋም የስርዓተ ጾታ ክበብ

1.1. የጾታ እና ሥርዓተ-ጾታ ፅንሰ ሃሳብ

“ጾታ” እና “ሥርዓተ ጾታ” ለሚሉ ቃላቶች ፅንሰ ሀሳብ እና ትርጉም አብዛኛውን ጊዜ በስህተት ብዙ ሰዎች በተለዋዋጭነት ሲጠቀሙባቸው ይስተዋላል። ነገር ግን ሁለቱ ቃላቶች የተለያየ ትርጉም ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

“ጾታ” የሚለው ቃል በሴት እና ወንድ መካከል የሚታዩትን የሥነ ተዋልዶ አካላት ልዩነት መኖርን ያመለክታል። ለምሳሌ

የጾታ እና ሥርዓተ-ጾታ ልዩነት ማሳያ ምሳሌዎች

የሥርዓተ ጾታ ማሳያ ምሳሌዎች፣

- ምግብ ማዘጋጀት የሴቶች ተግባር አድርጎ መውሰድ
- ወታደርነት ለወንዶች ብቻ የተሰጠ ሙያ አድርጎ ማየት፤
- ለማገዶ የሚሆን እንጨት መሰብሰብ የሴት ተግባር አድርጎ መውሰድ፤
- የሂሳብና ሳይንስ ትምህርቶች የወንዶች ብቻ አድርጎ ማየት፤
- እግር ኳስ ጫወታ ለወንዶች ብቻ የተሰጠ አድርጎ ማየት፤
- በቢሮ ውስጥ የጽህፈት ስራ ለሴቶች ብቻ የተሰጠ ተግባር አድርጎ ማየት፤
- የአመራርነት ስራ ለወንዶች ብቻ የተሰጠ አድርጎ መቁጠር፤

የጾታ ማሳያ ምሳሌዎች፣

የሴት ስነ ተዋልዶዊ አካል እና በሰውነት ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ቅመሞች (ሆርሞን) የተለዩ መሆን ፤ማርገዝ፤ መውለድ እና ጡት ማጥባት የሚያስችል ተፈጥሮ ያለ መሆኑን ያመለክታል ።በሌላ መልኩ የወንድ ሥነ ተዋልዶአዊ አካል የዘርፍሬን በማበርከት ከሴት የዘርፍሬ ከሆነው እንቁላል ጋር በመዋሃድ ሴት ወይም ወንድ ፅንስ እንዲፈጠር የማድረግ ተፈጥሮ ያለዉ መሆኑን ያመለክታል። በጣም አልፎ አልፎ የወንድ እና ሴት ስነ አካላዊ ተፈጥሮ (በተለምዶ ወንዳ-አገረድ ወይም ሴት-አገረድ የሚባሉ) ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነት ተፈጥሮ ያላቸው ሰዎች ቁጥራቸው ከ 1500 ሰዎች መካከል አንድ ሰው ብቻ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ።[1]

የአለም የጤና ድርጅት "ሥርዓተ ጾታ"ለሚለው ቃል የሰጠው ትርጉም አንድ የተወሰነ ማህበረሰብ ለሴቶች እና ለወንዶች ትክክል እና ተገቢ ናቸው ብሎ የሚሰጣቸው ሚናዎች፣ ባህሪያት፣ ተግባራት እና መለያዎች የሚያመለክት ሲሆን ሥርዓተ-ጾታ ከወንዶችና ሴቶች (ከተባዕትነትና ከእንስትነት) የሚጠበቁ ጠባዮችን፣ ችሎታዎችን፣ ተሰጥኦችን እና አይነተኛ ባህሪያትን የሚያካትት ትርጓሜ እንዳለው ያስቀምጣል።

የሥርዓተ-ጾታ ሚናዎችና ተጠባቂ ባህሪያት በልማድ የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ድርጊቶች በጊዜ ሂደት የሚለወጡ ከመሆናቸው ባሻገር በአንድም ሆነ በተለያዩ ባህሎች መካከል ልዩነት እንዳላቸው ይስተዋላል። በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ አቋም፣ የመደብ፣ የጎሳ፣ የአካል እና የአእምሮ ጉዳት፣ እድሜ እና የመሳሰሉት መለያዎች የስርዓተ ፆታ ሚናን ይቀርፁታል ።

የሥርዓተ-ጾታን ፅንሰ ሃሳብ ከማህበራዊ መስተጋብር አኳያ መቃኘት አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ስርዓተ ጾታ ላይ የሚንጸባረቀው ትርጉም በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ግንኙነት የተዛባ መሆኑን የሚያመለክት በመሆኑ ችግር ሆኖ እናገኘዋለን። ይሄውም በአብዛኛዉ ማህበረሰብ ዉስጥ ሴቶች የበታች፣ ወንዶች የበላይ መሆናቸውን በማሳየት እይታን ይገልጣል። ማህበረሰቡ በሴቶች ላይ የፈጠራቸው ዝቅተኛ አመለካከቶች ከተፈጥሮ የተወረሱና ቋሚ ቅርስ ሳይሆኑ በሂደት የሚለወጡና ሙሉ በሙሉ የሚጠፉ መሆናቸው በግልጽና በማያሻማ መልኩ መቀመጥ ያለበት ጉዳይ ነው።

በዘመናዊው ዓለም በአንዳንድ ማህበረሰብ ውስጥ ወንዶች ለዘመናት የሴቶች ተግባር አድርገው የሚቆጥሩዋቸውን ሥራዎች በመውሰድ እየተገበሩ የሚገኙ ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ሴቶች የወንዶች ተግባር አድርገው ሲቆጥሩዋቸው የኖሩትን ተግባራት እና ኃላፊነቶች በመውሰድ መተግበር ጀምረዋል። ይህ በጎ ጅምር በኢትዮጵያም ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ጉዳይ ነዉ።

1.2. ሥርዓተ-ጾታ እና ትምህርት: - የተገላቢጦሽ ተፅዕኖ

ሴት ልጆች ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት ከሚኖሩበት ማህበረሰብ የሚመነጩ ፈርጀ-ብዙ የሆኑ መዋቅራዊ እና ተቋማዊ እንቅፋቶች የሚያጋጥሟቸው መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ።

[1] Newman, Tim. "*Sex and Gender: What is the Difference?"* Medical News Today. *Feb* 2018. https://www.medicalnewstoday.com/articles/232363.php

የሴቶችን ትምህርት ከሚያሰናክሉ ምክንያቶች መካከል ጾታን መሰረት ያደረገ የማህበረሰብ ልማዳዊ ድርጊቶች በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸዉ ።በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ችግሮች ለሴቶች ትምህርት እንቅፋት ሆነው ይታያሉ። -

- በትክክለኛው እድሜ ላይ ትምህርት አለመጀመር፣
- በድህነት እና በሌሎች ችግሮች ምክንያት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በማጠናቀቅ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መሸጋገር አለመቻል፣
- የመሰረተ-ልማት አለመሟላት እንዳለ ሆኖ መሰረተ-ልማት በተሟላባቸዉ ትምህርት ቤቶችም ቢሆን የመሰረተ ልማት አቅርቦቶች ከስርዓተ ጾታ አንጻር የተቃኙ አለመሆናቸዉ፣
- በአብዛኛዉ ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደቱ ለስርዓተ ፆታ ጉዳዮች ምላሽ አሰጣጥን ሂደትና ተግባርን የተከተለ አለመሆን፣
- በትምህርት ቤቶች ውስጥ እና አካባቢ ስርዓተ ጾታ ተኮር ጥቃት በስፋት መኖር፣
- በተለይም በሴት ተማሪዎች/ልጆች ላይ የቤት ውስጥ የሥራ ጫና መኖር፣

በአብዛኛዉ የሀገራችን አካባቢዎች "ጋብቻ በተለየ ሁኔታ የሴትን ልጅ ክብር ከመጠበቅ አኳያ ያስፈልጋል" ከሚል የተዛባ አመለካከት ቤተሰብ የራሱን ዝና እና ክብር ለመጠበቅ ሲል ሴት ህጻናት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለዕድሜ ጋብቻ እንዲፈጽሙ ይገደዳሉ። ባለፉት ጥቂት አመታት ያለ ዕድሜ ጋብቻ የተወሰኑ መሻሻሎች አሳይቷል። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን በበርካታ የሀገራችን አካባቢዎች ያለእድሜቸው ጋብቻ የሚፈጽሙ ሴት ልጆች ቁጥር ከፍተኛ ነው። ሴት ህጻናት[2] ያለ ዕድሜቸዉ ወደ ጋብቻ እንዲገቡ በማድረግ በኩል በክልሎች መካከል ልዩነት ያለ ቢሆንም በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአምስት ልጃገረዶች ሁለቱ በህጻንነታቸው አግብተዉ ትዳር እንዲመሰርቱ ይደረጋሉ።[3]ይህ ሁኔታ ለሴት ተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል መሸጋገር እና ትምህርት የማጠናቀቅ ተግባር ላይ አሉታዊ ጫና ፈጥሯል።

ሴቶች በተለምዶ በህብረተሰቡ ውስጥ በሚሰጣቸው ዝቅተኛ ቦታ ምክንያት በቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤትና በአደባባይ ጾታዊ መድልኦ በሰፊው ይፈጸምባቸዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በአጠቃላይ ልጆች ስርዓት አክባሪ እንዲሆኑ በሚል አስተሳሰብ በወላጆች እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ አካላዊ ቅጣቶች በስፋት ይወሰድባቸዋል። ቁጥራቸው 30 ከመቶ የሚሆኑ እድሜያቸው ከ 11-17 የሆኑ ህፃናት ከመኖሪያ ቤታቸው ውጪ በመምህራን፣ በክፍል ጓደኞቻቸው እና በእድሜ አቻቸው አካላዊ ጥቃት እንደሚፈጸምባቸው ጥናቶች ያመለክታሉ።[4]

በትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ውጪ ሴት ልጆች ለጾታዊ ጥቃትና ትንኮሳ ሰለባ ሲሆኑ ወንዶች ደግሞ በአብዛኛው ለአካላዊ ቅጣቶች ተጋላጭ ናቸው። እነዚህ በተደጋጋሚ የሚፈጸሙ ጾታዊ መድልዎች እና ጥቃቶች በተለይም ሴት ልጆች ትምህርት ቤት ከመግባት ጀምሮ ትምህርት ማጠናቀቅ ድረስ ባለዉ የቆይታ ጊዜያቸዉ የትምህርት ተሳትፎአቸውን ክፉኛ ይጎዳዋል። በዚህም ምክንያት ከትምህርት ሊያገኙ የሚገባቸውን መሰረታዊና ተሸጋጋሪ ክህሎቶችን፣ በዜግነታቸው የነቃ ተሳትፎ እንዳያደርጉ፣ ራሳቸውን ለማብቃት እና የስራ እድሎችን ለመጠቀም እንዳይችሉ አድርጓቸዋል።

[2]ዕድሜአቸው ከ 18 አመት በታች የሆኑ ሁሉ ህጻናት ናቸው

[3]Ethiopia Demographic and Health Survey. 2016

[4]Parkes, Jenney et al. "Addressing SRGBV in Ethiopia: A scoping study of policy and practice to reduce gender-based violence in and around schools." *UCL Institute of Education.* 2017

በሌላ በኩል ትምህርት ተገቢ ያልሆነ የስርዓተ ጾታ መስተጋብርን ለማስተካከል ዓይነተኛ መሳሪያ መሆኑ በርካቶች የሚስማሙበት ሀቅ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ትምህርት ሴቶችን በትምህርት እና በኢኮኖሚ ለየማብቃት ከአለው ጠቀሜታ አንጻር ትኩረት እያገኘ በመሄዱ፤ በወንዶች እና በሴቶች መካከል የሚታየውን ተገቢ ያልሆነ የስርዓተ ጾታ መስተጋብርን ለመቀየር ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ ለሀገራቸው ዓመታዊ ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት (Gross Domestic Product) 10 በመቶ ድርሻ በእድሜ ዘመናቸው አስተዋፅዖ ሊያደርጉ እንደሚችሉ የአለም ባንክ ጥናት ያስረዳል።[5]

1.3. የሥርዓተ-ጾታ ክበብ ጠቀሜታ

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሃገራት ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖራቸው ዝቅተኛ አመለካከት ምክንያት የስራ ድርሻቸው በጓዳ ውስጥ እንዲወሰን አስገድዷል። ይህን ተከትሎ በርካታ ቤተሰቦች ሴት ልጃቸው በቤት በውስጥ ታናናሽ ውንድሞቻቸዉን እና እህቶቻቸዉን በመንከባከብ ሥራ እንድጠመዱ ያደርጋሉ።

ከዚህም የተነሳ ሴት ልጃቸው በቤት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜያት በማሳለፍ እና በአደባባይ ከማታውቃቸው ወንዶች ጓደኝነት እንዳትፈጥር ወላጆች ይጠብቃሉ።ብዙ ወንድ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት በሚሄዱበት ጊዜም ሆነ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ሴቶችን በመተንኮስ የሚያደርሱት ጉዳት እንዳለ አይገነዘቡም። ይህ የወንዶች ድርጊት በአቻ ጓደኞቻቸው ተቀባይነት ከማግኘቱ በተጨማሪ የጀግንነት መለያ ተደርጎ ይወሰዳል።

ይህን የተዛባ አመለካከት ማህበረሰቡ በመቀየር ዖታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን መቀነስ ብቻ ሳይሆን በሴቶች እና በወንዶች መካከል በመከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መፍጠር ያስፈልጋል።

ስለሆነም በእኛም ሀገር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሚገኙ የሥርዓተ ዖታ ክበብ በማጠናከር በሴት እና ወንድ ተማሪዎች መካከል ያለውን ትስስር አዎንታዊ እንዲሆን በማድረግ መልካም የሆነ የእርስ በርስ ግንኙነት ለመፍጠር የሚረዱ ክህሎቶችን በማጎልበት እንዲሁም ተጋላጭነትን በመቀነስና በማጥፋት ሴት ተማሪዎች በተገቢው ሁኔታ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉና እንዲያጠናቅቁ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

ምንም እንኳን በሀገራችን በትምህርት ቤቶች የሚገኙ የሴት ተማሪዎች ክበባት፤ ሴት እ ናወንድ ተማሪዎችን እኩል ስለማገልገላቸው የሚያሳይ ማስረጃ ውስን ቢሆንም የሴቶችን ትምህርት ከማጎልበት አኳያ የድርሻቸዉን አስተዋጽኦ እያበረከቱ መሆኑ ይታመናል። ይህን እንጂ የስርዓተ ጾታ ክበብ በሚል

በጋና ሀገር ከልጃገረዶች ክበብ ውጤታማነት የተወሰደ ልምድ

በጋና ሀገር በትምህርት ቤቶች የሴት ተማሪዎች ክበብ አባላት በክበባቱ በመሳተፋቸው ምክንያት ትምህርት እንዳያቋርጡ እግዚቸዋል፤፣ በዋነኛነትበክበቡ በሚሰጣቸዉ የህይዎት ክህሎት ስልጠና ምክንያት ሃሳባቸውን በግልጽ ማቅረብችለዋል፣ በራስመተማመናቸው የጨመረ መሆኑ ተመልክቷል፣ተጽእኖ ፈጣሪም ሆነዋል።

በአንዳንድ ርዕሶች ላይ ወንዶች ከሴቶች ጋር በመሆን ስልጠና እንዲሰጠቻዉ ባሳዩት ፍላጎት መሰረት ስልጠናዉን ያገኙ ወንዶችም ቀደም ብሎ የነበራቸዉ ባህሪያት ከመለወጡ ባሻገር ለሴቶች ትምህርት የሚሰጡት ክብር ጨምሯል።

በተጨማሪ በቤት ውስጥስራዎች ከሴቶች ጋር ተጋርቶ በመስራት ላይ መሻሻል አሳይተዋል። መምህራንምሴቶች ከልጅ ተንከባካቢነት እና የወደፊት ሚስትነት የዘለለ ሚና አይኖራቸዉም የሚለዉ አመለካከታቸዉ እየተቀየረ መምጣቱ ታይቷል።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ 2017 ዓ.ም በተካሄደ የሴት ተማሪዎች ክበብ መርሃ-ግብር ግምገማ እና ክለሳ ላይ ለሴቶች ተብለዉ በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ውጭ የተከናወኑ ፕሮጀክቶችን የክበባቱ አዎንታዊ ውጤቶች ላይ ተጨማሪ ማስረጃ አቅርቧል። የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

[5]The World BanK, Measuring the Economic Gain of Investing in Girls the Girl Effect Dividened, 2011

- አግላይ የሥርዓተ ጾታ ልማዶች እና ድርጊቶች ላይ የመጣ ለውጥ

ስያሜ እንዲደራጅ በማድረግሴትና ወንድ ተማሪዎች ፍትሃዊ ግንኙነት እንዲኖራቸዉ በማድረግ እና የአብሮነት ባህል በማዳበር የጾታ እኩልነትን ለማስፈን የሚደረገዉን ጥረት ለማጎልበት እንደሚቻል መገመት ይቻላል።

የሥርዓተ ፆታ ክበብ ሰብአዊ መብቶች ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ፣ የመማር ክህሎቶችን ለማጎልበት፣የህጻናት ጋብቻን እና ጾታዊ ጥቃት ለመከላከል እንደ መደላድል በመሆን ይረዳል።በተጨማሪ ጾታዊ ጥቃት ተከስቶ በሚገኝበት ጊዜም ከሚመለከታቸው የፍትህ ፤የጤና እና ከሌሎችም ባለድርሻዎች ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንደመነሻ ይጠቅማል።

ክፍል ሁለት፡

በኢትዮጵያ የሥርዓተ ጾታ ክበብ በትምህርት ቤቶች ማቋቋም ዓላማ እና መርህዎች፤

2.1.የሥርዓተ-ጾታ ክበብ ነባራዊ ሁኔታ፡ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ አሁን በየትምህርት ቤቶቹ ለተቋቋሙት የሥርዓተ ፆታ ክበባት መነሻ የሴት ተማሪዎች ክበባት ሲሆኑ፤ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ እና ውጤታማነት ከማጎልበት አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በ 2010 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር የስርዓተ ጾታ ዳይሬክቶሬት በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች የስርዓተ ጾታ ክበባት እንቅስቃሴ ለመገምገም በተከናወነ የክትትል እና ድጋፍ ሥራ በክበባቱ በኩል የሚከናወኑ ተግባራት ከዚህ በታች በቀረበዉ መሰረት በሪፖርቱ ተመልክቷል።

- ለሴት ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ ፤
- ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ካላቸዉ ቤተሰቦች ለሚመጡ ሴት ተማሪዎች የገንዘብ እና ቁሳቁስ እገዛ ማድረግ ፤
- ለሴት ተማሪዎች የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ማቅረብ ፤
- ጾታዊ ጥቃትን የመከላከል እና ምላሽ የመስጠት ስራ ማከናወን ፤
- የልጅነት ጋብቻንና ጠለፋን እንዲቋረጥመደረጉ፤
- ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለሱ መደረጉ፤
- አልፎ አልፎም ቢሆን በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የህይወት ክህሎት ስልጠና መስጠትዋናዎቹ ተግባራት ናቸው።

“ጌጅ” (Gender and Adolescence Global Evidence) የሚባል ድርጅት ኢትዮጵያን ጨምሮ በበርካታ ሀገራት

ግለ ታሪክ ፡ የስርዓተ ጾታ ክበብ የልጅነት ጋብቻን ላይ ምክር በመስጠጥ በኩል የሚጫወተዉ ሚና ምንድን ነዉ;

ባለፈዉ ዓመት የ 14 አመቷ አይሻ ታላቅ ወንድሜ ጋብቻ እንድትፈጽም ተጠየቀች። የአይሻንድም እንድታገባዉ የጠየቃት ሰዉ በ 10 ዓመት ዕድሜ የሚበልጣት እና የወንድሟ ጓደኛዉ የነበረዉ ሰዉ ሲሆን ይህ ሰዉ አይሻን በ 10 ዓመት ይበልጣታል። አይሻ ይህን ታሪክ ስትናገር እንድህ አለች። እኔን ቤተሰቦቼ ሊድሩኝ በተጠየኩበት ወቅት ጥያቄዉን ተቃወምኩኝ። በዚህ ተግባሬም ከቤተሰቦቼ ጋር ከፍተኛ የሆነ እስጥ አገባ ዉስጥ አስገባኝ። ለጊዜዉ ይህ ችግር ግራ ቢያጋባኝም በትምህርት ቤታችን የተቋቋመዉ የስርዓተ ጾታ ክበብ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰራ መሆኑ አስታወስኩ እና ወደ ትምህርት ቤት በመሄድ ወድያዉኑ ለክበቡ አስተባባሪ ችግሬን ሪፖርት አደረኩኝ። ትምህርት ቤቱም መብቴን ለማስከበር ከእኔ ጎን እንደሚቆም በማሳወቅ ወንድሜ ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጣ በማድረግ ስለ ተፈጠረዉ ችግር ለመወያየት ቀጠሮ ተያዘ። በመጨረሻም ወንድሜ የቀረበለትን ጥያቄ ተቀብሎ ያቀረበልኝን የጋብቻ ጥያቄ ለመሰረዝ በመስማማቱ እኔም መብቴን አስከብሬ ትምህርቴን ለመከታተል በቃሁ። አሁን እኔ 7 ኛ ክፍል በመማር ላይ የምገኝ ተማሪ ነኝ.” (UNICEF Ethiopia, 2019)

ያካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው በትምህርት ቤቶች የሚገኙ የሴት ተማሪዎች ክበብ ማቋቋም እና ወደ እንቅስቃሴ እንዲገቡ መደረጉ ትምህርት ቤትን መሰረት ካደረጉ መርሃ ግብሮች መካከል በዋነኝነት የሚጠቀስ ተግባር ነዉ። እነዚህ ክበባት የሴቶችን የመማር ውጤት ማሻሻል እና ደህንነታቸውን ማስጠበቅ በትኩረት የሚያከናዉኑዋቸዉ ተግባራት ሲሆኑ በተጨማሪ በአካባቢያቸዉ ከሚገኘዉ ማህረሰብ እና አመራርጋር የተሳካ ግንኙነት በመፍጠር የሚንቀሳቀሱ መሆኑ ተመልክቷል።

ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ እንደሚያሳየው የሴት ተማሪዎች ክበባት በስነ ተዋልዶ እና በሴቶች ህጋዊ መብቶችላይ ማህበረሰቡ በቂ ግንዛቤእንዲኖረዉ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።በተመሳሳይ ሁኔታክበባትታዳጊ ወጣት ሴቶች ከአፍላ እድሜ ጀምሮ ስለሚከሰተዉ የወር አበባ አጠባበቅ ግንዛቤቸዉን ለማሳደግ አስተዋጽኦ አድርጓል። ክበባት የትምህርት ተሳትፎና ውጤትን ከማሳደግ እንዲሁም መጠነ ማቋረጥን ከመቀነስ አኳያ አስተዋጽኦ ማድረጋቸዉ፤ ትምህርት ያቋረጡ ሴቶች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለሱ ለማድረግ እና ያለፋቸዉን የትምህርት ክፍለ ጊዜያት የማካካሻ ትምህርት ፕሮግራም በማመቻቸት እንዲማሩ ከማድረጋቸዉ በተጨማሪ የትምህርት ወጪን ለመሸፈን የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

ምንም እንኳን በበቂ ማስረጃ ማስደገፍ አዳጋች ቢሆንም በሀገራችን በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሴት ተማሪዎች ክበባት ውጤታማነት ላይ ተቃራኒ ሃሳቦች ሲሰነዘሩ ይስተዋላል። አንዳንድ ሰዎች ክበባት የሴቶች አቅም ከማሳደግ አንጻር ያላቸውን ሚና በበጎነት የሚያዩት ሲሆን በአንፃሩ ሌሎች ሰዎች ከፋይዳ፣ ተደራሽነት፣ ዘላቂታዊነትና ወጪ ቆጣቢነት አኳያ ጥያቄ ያነሳሉ።[6]

በሥርዓተ ፆታ ክበብ የሚደረጉ የድጋፍ አሰጣጥ እና ደረጃዎቹ ከአንዱ ትምህርት ቤት ወደ ሌላዉ ትምህርት ቤት ስንሄድ ዉጤታማነታቸዉ የሚለያይ ቢሆንም በአጠቃላይ ሲታይ ግን እንቅስቃሴቸዉ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እና በክበቡ ተጠሪ መምህር ጥንካሬና ቁርጠኝነት ላይ የተመሰረተ ነው።

በተመሳሳይ ጊዜ የተከናወነዉ የክትትል እና ድጋፍ ስራ በሀገራችን በሚገኙ የሥርዓተ ጾታ ክበባት እንቅስቃሴ ላይ የሚታዩ ክፍተቶች፡-

- በትምህርት ቤቶች የተቋቋሙ ክበባት ጠንካራ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዲችሉ በየደረጃዉ ከሚገኙ አካላት በአብዛኛው በቂ ድጋፍ እና ክትትል ያለመደረጉ፤
- የክበባቱ የእቅድ ዝግጅት እና ትግበራ ሂደት ባለድርሻዎችን ባሳተፈ መልኩ እና አሰራሩን ተከትሎ አለመከናወኑ፤
- የስርዓተ ጾታ ክበባት ለሴት ተማሪዎች ብቻ የተቋቋሙ አድርጎ በመውሰድ የወንዶች ተሳትፎ ማነስ ወይም ሙሉ በሙሉ አለመኖር፤
- የጾታ እኩልነትን ለማስፈን ተብለዉ የተቋቋሙ ክበባት ወጥነት ያለዉ ተግባር አለማከናወን እንደተጠበቀ ሆኖ የተግባራት ድግግሞሽ እና የሚና ግጭቶች በስፋት ተስተውለዋል።ለምሳሌ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ “የልጃገረዶች መድረክ” ፣ “የሥርዓተ ፆታ ክበብ” ፣ “የልጃገረዶች ክበብ” ፣ “የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያ ክበብ” በሚል ቢደራጁም ተግባር እና ሃላፊነታቸው በአመዛኙ ተመሳሳይ መሆኑን ማየት ተችሏል የሚሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።[7]

[6] Rachel Marcus, Nandini Gupta-Archer, Madeleine Darcy and Ella Page, September 2017- GAGE

[7] ትምህርት ሚኒስቴር 2010

2.2. በመመሪያዉ ዉስጥ ለሥርዓተ-ጾታ ክበብ የተሰጠ ትርጉም

በሀገራችን ባሉ ትምህርት ቤቶች የሥርዓተ ፆታ ክበባት ወጥነት እና ግልጽነት ባለው መልኩ ለማቋቋምና ለመምራት ክፍተት በመኖሩ ትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ፆታን ፅንሰ ሃሳብ ትርጉም እንደሚከተለው አስቀምጧል።

> የሥርዓተ ፆታ ክበብ በአንድ ትምህርት ቤት የሚማሩ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች ለአንድ ዓላማ በቡድን ተደራጅተዉ የሚንቀሳቀሱበት መድረክ ነዉ።፤ ይህ መድረክ ተማሪዎች የጾታ እኩልነት ማስፈንን በተመለከተ በክፍል ውስጥ በመደበኛ የስርዓተ ትምህርት ፕሮግራም የሚማሩትን ትምህርት ለማጠናከር ተብሎ የሚቋቋም ሲሆን ተግባሩም ለሴትና ወንድ ተማሪዎች መረጃ በመስጠት እና ክህሎታቸዉን በማጎልበት የተዛባውን የስርዓተ ጾታ መስተጋብር በማስተካከል እንዲሁም የሴቶችን እኩል ተሳትፎ በማበረታታት ስለ ጾታ እኩልነት እንዲማማሩበት የተፈጠረ መደላድል ነዉ።፤፤ ከዚህ በተጨማሪ ሴት ተማሪዎች በጾታቸው የሚደርስባቸውን ችግሮች ለማስወገድ የሚደረጉ ጥረቶችን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር እና የመማር ተግባርን በማጎልበት የግል ብቃትን ማሳደግ ተማሪዎች የወደፊት የስራ ዕድላቸውን በማስፋት በመጨረሻም ንቁ ዜጎች ለመፍጠር የሚያስችሉ ስራዎች በትምህርት ቤት ደረጃ የሚከናወንበት መድረክ/ መደላድል ነዉ።

2.3 የሥርዓተ-ጾታ ክበብ ዓላማዎች

በትምህርት ቤት ደረጃ የሥርዓተ ፆታ ክበብ በማጠናከር ተማሪዎች ስለ ጾታ እኩልነት በክፍል ዉስጥ የሚማሩትን ወደ ተግባር ለመቀየር ያለዉ ጠቀሜታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ ትምህርት ሚኒስቴር ይህን የሥርዓተ-ፆታ ክበባት ማቋቋሚያና ማጠናከሪያ መመሪያ አዘጋጅቷል።

አጠቃላይ ዓላማ፤-ሴት እና ወንድ ተማሪዎች የጾታ እኩልነት ማስፈንን በተመለከተ ዘላቂና ውጤታማ የሆነ የእርስ በርስ መወያያ መድረክ በመፍጠር ፍትሃዊ ግንኙነትን ማቀላጠፍ፤ አካታችነትን ማበረታታት፤ሴት እና ወንድ ተማሪዎችን በማብቃት የተዛቡ የሥርዓተ ጾታ ሚናዎች እና ተግባሮችን ማስተካከል ነው።

ዝርዝር ዓላማዎች፡

- **ሴት እና ወንድ ተማሪዎች እርስ በራሳቸው እንዲከባበሩ እና ግንኙነታቸው በእኩልነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ፤**
- **በስርዓተ ጾታ ተግዳሮቶች እና መፍትሄዎቻቸው ላይ የውይይት መድረክ ለመፍጠር**
- **መልካም አርአያ የሆኑ ሴትና ወንድ ተማሪዎችን ማፍራት፤**
- **የመረጃ የእውቀትና የክህሎት ማሻሻ መድረኮችን በመፍጠር ሴትና ወንድ ተማሪዎችን ማብቃት፤**
- **የጾታ እኩልነትን ለማስፈን በትምህርት ቤት እና ውጭ ባሉ የህብረተሰብ መዋቅሮች ግንዛቤ እና ንቅናቄ መፍጠር፤**
- **በትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ውጭ ካሉ መዋቅሮች ጋር በመቀናጀት ጾታዊ ጥቃትን እና የልጅነት ጋብቻን መከላከል፤**
- **በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የመማር ማስተማር ሂደት ለሥርዓተ ፆታ ጉዳዮች ምላሽ እንዲሰጥ ማድረግ።**

2.4. የሥርዓተ-ጾታ ክበብ መርሆዎች

ይህ የሥርዓተ ፆታ ክበብ መመሪያ የሚከተሉት መሰረታዊ መርሆዎች አሉት።

ሀ) አባል ለመሆን ሁሉም እኩል መብት ያለዉ መሆኑ፤



ማንኛዉም ፍላጎት ያለዉ ሴት ወይም ወንድ ተማሪ እንዲሁም ሌሎች የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት በፆታ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በብሔር/በጎሳ፣ በኑሮ ደረጃ ልዩነት ሳይደረግባቸው የሥርዓተ ፆታ ክበብ አባል የመሆን መብት አላቸው።

ለ) ሀሳብን በነፃነት መግለፅ፤

የሥርዓተ ጾታ ክበብ አባል በመሆን የሚሳተፉ ሁሉ ሃሳባቸውን በነፃነት የመግለፅ መብታቸው የተጠበቀ ነው።

ለሥርዓተ ፆታ ክበባት ስኬት በአጠቃላይ የተማሪዎች ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በውይይት ጊዜ ሴቶች እና ወንዶች ሃሳብባቸዉን በነጻነት በመግለፅ እኩል ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ሐ) የክበቡን ደንብ ማክበር፤

አባል የክበቡን ደንብ የማክበር ግዴታ አለበት/አለባት፤ በተጨማሪም ለራስ እና ለሌሎች የሚሰጠውን ክብር በተግባር ማሳየት ይጠበቅበታል/ይጠበቅባታል።

መ) ጾታን መሰረት ያደረገ አድልዎና መገለልን አለመታገስ፤

የሥርዓተ ፆታ ክበብ አባላት በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሚኖር አድሏዊነትን፣ ጎጂ ተግባራትን፣ በሃይማኖቶች መካከል የሚደረግ ልዩነትን፣ የተዛባ የሥርዓተ ፆታ መስተጋብርን፣ አካል ጉዳት ያለባቸውን ወገኖች ማግለልን፣ እና የመሳሰሉ ተግባራትን መታገስ የለባቸውም።

ሠ) በውይይት ማመን፤

አለመግባባትን ወይም ግጭትን ለማስወገድ የውይይት ባህልን ማዳበር ወሳኝ ነው።

ረ) ጊዜ እና ሌሎች ሀብቶችን በአግባቡ መጠቀም፤

አባላት በውይይት ወቅት ለክበቡ ፋይዳ በሌላቸው አልባሌ ጉዳዮች ውድ ጊዜያቸውን ማባከን የለባቸውም። ሁሉም ውይይቶች በክበቡ አላማዎች ዙሪያ ያውጠነጠኑ መሆን ይገባቸዋል።

በትምህርት ቤቱ እና ከትምህርት ቤት ውጭ ባሉ የማህበረሰብ አባላት ተቀባይነት የማግኛ ዘዴ

የሥርዓተ ፆታ ክበብን እንቅስቃሴን ውጤታማ ለማድረግ አራት ዋና ዋና ተግባራት ማከናወን ይጠበቃል።

እነርሱም: -

1. ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ፤- ይህ ተግባር ለመምህራን፣ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለሌሎች የማህበረሰቡ አባላት በክበቡ አስፈላጊነት እና ጥቅም ላይ ግንዛቤ ማስጨበጥን ያካትታል። ወላጆች፤መምህራን እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ሴት ተማሪዎች ከክበቡ የሚያገኙት ዕውቀትና ክህሎት የትምህርት ተሳትፎቸውን ከማጎልበት ባሻገር ውጤታማ እንዲሆኑ የሚረዳ መሆኑን ማስገንዘብ ይገባቸዋል፤
2. በክበቡ ከሚሳተፉ መምህራን እና ተማሪዎች መካከል በምሳሌነት የሚጠቀሱትን መለየት፤- ይህ ተግባር በክበቡ ቀጣይነት ላይ ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ በምሳሌነት የሚጠቀሱ አባላት ተግባር በማስተዋወቅ ሌሎች እንዲከተሉ ማድረግ ይጠበቃል፤
3. የሥርዓተ ፆታ ክበብ መሰረታዊ መርሆዎችን እንዲገነዘቡ ማድረግ፦ የሥርዓተ ፆታ ክበብ በቀጥታ በክፍል ውስጥ የሚከናወን ተግባር ሳይሆን መምህራን፤ የክበቡ አስተባባሪዎች እና አመቻቾች እንደ ክፍል ውስጥ የትምህርት ስራ ውጤት እና ግምገማ አባላትን መፈተን አይገባቸውም። ይልቁንስ አባላት እንዴት ያገኙትን ክህሎት ወደ ስራ እንደሚተረጉሙ እና የስርዓተ ጾታ መስተጋብር ጤናማነት ላይ በማተኮር ድጋፍ መስጠት፤
4. የሥርዓተ ፆታ ክበብ እንቅስቃሴን ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ማድረግ፤- የክበብ አባላት እና አመራር የስርዓተ ጾታ እኩልነት እና መስተጋብር በተመለከተ ያለውን ልምድ ዕውቀት እና ክህሎት ለሌሎች አባል ላልሆኑት የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እና በውጭ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት መስጠትይጠበቃል፤

ክፍል ሶስት፡

የሥርዓተ ጾታ ክበብ አደረጃጀት፤ አመራር እና አሰራር

3.1.አባልነት

የሥርዓተ ጾታ ክበብ አባልመሆን በግል ፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን አብዛኛው ሴት እና ወንድ ተማሪዎች በአባልነት እንዲሳተፉ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። ክበቡ ሴት ተማሪዎች በትምህርት ስራቸዉ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ከማስወገድ በተጨማሪ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በሴቶች ላይ ተንሰራፍቶ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት ከአለዉ ፋይዳ በመነሳት ሴት ተማሪዎች ወደ አባልነት እንዲመጡ በማድረግ የዕድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በልዩ ትኩረት ሊሰራ ይገባል።

በአጠቃላይ የስርዓተ ጾታ ክበብ አባል የሚሆኑ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች ዕድሜያቸው ከ 10 እስከ 19 ዓመት ውስጥ የሚገኙ ይሆናሉ። ምክንያቱም በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች ለተለያዩ ስርዓተ ጾታዊ ችግሮች ተጋላጭ በመሆናቸው ነው። ነገር ግን ሌሎች ከዚህ የዕድሜ ክልል በታች እና በላይ የሆኑ ሴትና ወንድ ተማሪዎች አባል የመሆን መብታቸው የተጠበቀ ነው።

የክበብ አባልነት ምዝገባ እና የአባላት ቁጥር

- ፍላጎት ያላቸዉ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች የክበብ አባል መሆን የሚችሉ ሲሆን ሌሎች የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባል የሆኑም አባል መሆን ይችላሉ።
- የክበብ አባላት ቁጥር መወሰን አይቻልም፤፤ ማንኛዉም ፍላጎት ያለዉ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባል የሆነ ሁሉ የክበብ አባል የመሆን መብት እስካለዉ ድረስ፣ ይሁን እንጂ የክበብ አባላትን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በመዉሰድ በንዑስ ቡድኖች እንዲደራጁ ማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ ያክል የወር አበባ ማየት የጀመሩ ኮረዳ ሴት ተማሪዎች ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸዉ በመሆኑ በአንድ ቡድን እንዲደራጁ ማድረግ ይቻላል።
- በንዑስ ቡድን የሚደራጁ የክበብ አባላት ቁጥራቸዉ ከ 20-40 ማድረግ ይቻላል። .
- በንዑስ ቡድን የሚደራጁትን የክበብ አባላት እንደአስፈላጊነቱ በጾታ ሊለያዩ ይችላሉ። ይሄዉም ለምሳሌ ሴት ተማሪዎች ስለ የወር አበባ አጠባበቅ ለማስተማር ሲፈለግ ወንዶች በዚህ ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ማድረግ አስፈላጊ ባለመሆኑነዉ። ይሁን እንጂ በወር አበባ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ለመስራት ሲፈለግ ወንዶችም እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል።

3.1.1. ምዝገባ

በትምህርት ቤቱ በመልካም አርዓያነት የሚጠቀሱ ሴትና ወንድ ተማሪዎች የክበቡ አባል እንዲሆኑ በማድረግ ሌሎች ተማሪዎች የማነሳሳት ስራ በማከናወን የአባላትን ቁጥር በተፈለገው መጠን ማሳደግ ይገባል። የአባላት ምዝገባ በትምህርት ዓመቱ የመጀመሪያ ወር መጠናቀቅ ያለበት ሲሆን የምዝገባ ስራው የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም ይሆናል።ለምሳሌ (የሰንደቅ ዓላማ ስነ-ስርዓት፣ በክፍል ውስጥ በመገኘት፤ በሚኒሚድያ በመጠቀም፤ በማስታወቂያ ሰሌዳ እና ቢልቦርድ ወዘተ) በቂ ቅስቀሳ በዘመቻ መልክ ከተካሄደ በኃላ ምዝገባ ማካሄድ ያስፈልጋል።

የምዝገባ ስራዉ በተለያዩ ምክንያቶችተጋላጭ የሆኑ (አካል ጉዳተኞች፤ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው፤ ዝቅተኛ የገቢ ምንጭ ካላቸው ቤተሰብ የመጡ፤ኤች. አይቪ. ኤድስ ያለባቸው፤በተለያዩ ምክንያት ወላጆቻቸዉን ያጡ ወዘተ) ሴትና ወንድ ተማሪዎች መረጃ የማግኘት ዕድላቸው ጠባብ ስለሆነ እነዚህን ለመድረስ እና በአባልነት ለማካተት የተለየ ትኩረት ተደርጎ ሊሰራበት ይገባል።

3.2. አደረጃጀት

ትምህርት ሚኒስቴር ተጓዳኝ ክበባትን በተመለከተ ባዘጋጀው *መመሪያ* በግልፅ እንደተመለከተው የተጓዳኝክበባትን የማደራጀት ሃላፊነት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ሲሆን **ክበባቱ ተጠሪነታቸው ለትምህርት ቤቱ የአካዳሚክ ምክትል ርዕሰ መምህር መሆን ይጠበቅበታል።**

በመሆኑም የሥርዓተ ፆታ ክበብ ሪፖርቱን **ለትምህርት ቤቱ የአካዳሚክ ምክትል ርዕሰ መምህር ማቅረብ የሚጠበቅ** ሲሆን ነገር ግን **ትምህርት ቤቱ ባለው አደረጃጀት ምክንያት ምክትል ርዕሰ መምህር ከሌለው ሃላፊነቱ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ላይ ይወድቃል።** የሥርዓተ ፆታ ክበብ አስተባባሪ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር የመሰየም ስራ የሚከናወን ሲሆን ክበቡን የማስተባበር ስራ ለጊዜዉ ለሴት መምህራን ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ለአስተባባሪነት የምትሰየመዉ ሴት መምህርት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባታል።

- በስነ ምግባር የታነፀች፣ ሀቀኛ እና ሰው አክባሪ የሆነች፤
- ለፆታ እኩልነት በቁርጠኝነት የምትታገል፤
- ለሌሎች አርአያ የሆነች፤

የክበቡ ሰብሳቢ በሥርዓተ ፆታ ክበብ ጠቅላላ ጉባኤ የምትመረጥ ሲሆን በትምህርት ቤቱ መልካም አርዓያ ያላት ሴት ተማሪ መሆን አለባት። የክበብ አስተባባሪዋ መምህርት የስራ ዘመን ከሁለት እስከ ሶስት ዓመት ሲሆን በድጋሚ ተሰይማ ልትሰራ ትችላለች።

በተለያዩ ሀገሮች ለክበብ አባልነት ለመሆን የሚቀርቡ መስፈርቶች

ኢ.ቪ.ፍ.ኢ -ኬንያ
- የዕድሜ ክልል: ታዳጊ ወጣቶች 10-16 እድሜ
- ምዝገባ፤ ግዴታ ነዉ
- መስፈርት: ችግረኛ የሆኑ ህጻናት የቅድሚያ ይኖራቸዋል
- ጾታ: ሴቶችም ወንዶችም
- ክበብ እንቅስቃሴ: ሴቶችና ወንዶች ለየብቻቸዉ እንዲወያዩ ወይም እንዲንቀሳቀሱ ይደረጋል
- አባላት ተለያይተዉ እንዲንቀሳቀሱ የሚደረግበት ምክንያት : እንደ ርእሰ ጉዳዩ የሚወሰን ይሆናል።

ኢ.ች.ኦ.ፒ.ኢ. (ሀይቲ Pwoje Espwa)
- የዕድሜ ክልል 10-24 ዕድሜ
- ጾታ: ሴቶች ብቻ
- ትኩረት:በትምህርት እና ከትምህርት ቤት ዉጭ የሚገኙትን ያጠቃልላል
- ቦታ: ከተማ ዉስጥ ወይም አካባቢ
- መስፈርት: ወላጆቻቸዉን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡ ህጻናት

(Source: Source: “A Practical Handbook for Creating and Leading a Girls’ Club.” *WomenStrong International*. 2018)

የክበቡ ሰብሳቢ፣ ፀሀፊ እናየስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ ሲሆን ለሥርዓተ ፆታ እኩልነት በቁርጠኝነት የሚታገሉ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርበታል። የሥራ ዘመናቸውም አንድ ዓመት ሲሆን ጠቅላላ ጉባኤው ካመነባቸው በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ።

የስርዓተ ጾታ ክበብ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አመልካች ሰንጠረዥ



3.2.1. የስርዓተ ጾታ ክበብ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት

- የክበቡ አስተባባሪ---------- ሴት መምህርት
- የክበቡ ሰብሳቢ---------- ሴት ተማሪ
- ጸሀፊ----------ሴት ወይም ወንድ ተማሪ
- የክበቡ አባላት---------- መምህራን (አንድ ሴት እና ወንድ)

3.3. አመራር

3.3.1. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፣ተግባር እና ሃላፊነት

የስርዓተ ጾታ ክበብ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን ተግባር እና ኃላፊነት ይፈጽማሉ።

- የክበቡን እንቅስቃሴ በበላይነት መምራት፣
- የክበቡን ቢሮ፣ የስራ ማስኪያጃ በጀትና ሌሎች ቁሳቁሶችን ከትምህርት ቤቱ አመራር ጋር በመሆን በማሟላት ወደ ሥራ መግባት፣
- የክበቡን ዓመታዊ ዕቅድ ረቂቅ በማዘጋጀት እና በጠቅላላ ጉባዔ በማጸደቅ ለትምህርት ቤቱ አመራር ማቅረብ፣
- ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የሩብ ዓመቱ በማካሄድ የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ ማካሄድ፣
- አርአያነት ያለው ስራ ላከናወኑ የክበብ አባላት የእውቅና አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ።

የክበቡ አስተባባሪዋ ተግባር እና ኃላፊነት

ከላይ እንደተጠቀሰዉ የክበቡ አስተባባሪ ሴት መምህርት ስትሆን ተጠሪነቷ ለአካዳሚክ ምክትል ርዕሰ መምህር/ት ሆኖ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሯታል።

- በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ወር ላይ የክበቡ መርሀግብች መሰረት አባላትን መመዝገብ፣

- በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በመመሪያዉ መሰረት ለአባልነት ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል ስብሳቢዋን ጨምሮ ሌሎች የስራ አስፈጻሚ አባላትን አቅጣጫ ማስያዝ፤
- የክበቡን አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች በመምራት አቅጣጫ ማስያዝ፤
- የክበቡ ስብሳቢ እንቅስቃሴ በመምራት አቅጣጫ ማስያዝ፤
- በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መካከል የሚከሰቱ ልዩነቶችን መፍታት፣
- ከትምህርት ቤቱ አመራርና አስተዳደር ጋር በመመካከር ለክበቡ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማሟላት፣
- ከትምህርት ቤቱ አመራር ጋር በመመካከር ከባለድርሻ አካላት እና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የስራ ግንኙነት ማድረግ፤
- ክበቡ ተግባራቱን በእቅዱ መሰረት መፈፀሙንመከታተል፤መደገፍ እና ማረጋገጥ፤

የክበቡ ስብሳቢዋ ተግባር እና ኃላፊነት

የክበቡ ስብሳቢተጠሪነቷ ለክበቡ ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ታከናውናለች።

- የክበቡ አስተባባሪ በምትሰጣት አስፈላጊ የሆኑ አቅጣጫዎች እና ምክር መሰረት ክበቡን በበላይነት መምራት፣
- የስብሰባ አጀንዳ በመቅረጽ ጠቅላላ ጉባኤና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ስብሰባ መጥራት፣
- ስብሰባውን መምራት እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት፣
- የክበቡን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባዔ ማስጸደቅና ሥራ ላይ ማዋል፣
- **የክበቡን የዕቅድ ዝግጅት ሂደት ማስተባበር፣ መከለስ እና** በጠቅላላ ጉባዔ ማስጸደቅ፣
- **የክበቡን የቅስቀሳና የማስተዋወቅ ተግባር በበላይነት መምራት፣**
- **እንደየስፈላጊነቱ ከሌሎች ክበባት ጋር በትብብር መስራት፣**
- **የሩብ ዓመት፣የግማሽ አመትና የዓመቱን የስራ ክንውን ሪፖርት ለክበቡ አስተባባሪ** ማቅረብ፣
- **ከክበቡ አስተባባሪ መምህርት ጋር በመመካከር ክበቡን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን።**

የክበቡ ፀሀፊ ተግባር እና ኃላፊነት

- ስብሳቢዋ በሌለችበት ጊዜ የክበቡን እንቅስቃሴ መምራት፣
- የአባላትን መረጃ፣ መዝገብ እና ሌሎች የክበቡን ሰነዶች በአግባቡ መያዝ፣
- የስብሰባ ቃለ ጉባኤ መያዝ፤

የክበቡ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ተግባር እና ኃላፊነት

- የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት፣ ሀብት በማፈላለግ ችግረኛ ተማሪዎች ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፤
- የክበቡን ስራ ማስተዋወቅ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት፤
- ተግባር ተኮር ጥናትና ምርምር ስራ ማስተባበር፤
- በክበቡ እንቅስቃሴ ውሳኔ ለመስጠት የሚያግዙ አስተዳደራዊ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን መሰብሰብ እና ማደራጀት፤

የንዑስ ቡድኖች አመቻቾችን መምረጥ

- ንኡስ ቡድኖች ከተቋቋሙ በኃላ ለንዑስ ቡድን አመቻች አባላት ከመካከላቸው ይመርጣሉ።
- የንኡስ ቡድን አመቻች የውይይት መድረኮችን በተቀናጀ ሁኔታ መምራት
- በስብሰባ ወይም በስልጠና የሚገኙ እና የማይገኙ አባላትን መቆጣጠር
- የተለያዩ መዝሙሮች በማዘጋጀት ለማነቃቂያነት መጠቀም
- የእያንዳንዱን እንቅስቃሴ ሪፖርት ለዋናዋ ሰብሳቢ ማቅረብ
- እንደ የአስፈላጊነቱ ንዑስ ቡድኖች ለአባላቶቻቸው የተለያየ ኃላፊነቶችን ያከፋፍላሉ።
- ሁሉም የንኡስ ቡድኑ እንቅስቃሴዎች በስርዓተ ጾታ ክበብ አመራር ሱፐርቫይዝ ይደረጋሉ።

3.3.2. የስብሰባ ጊዜ፣ የጠቅላላ ጉባዔ

በትምህርት ዘመኑ የመጀመሪያ ወር (መስከረም)ላይ ዓመታዊበቅድ ለማጽደቅእንዲሁም በዓመቱመጨረሻ (ሰኔ) ወርየዕቅድ አፈፃፀምግምገማ ለማካሄድ የክበቡየጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የሚከናወን ይሆናል።

የስርዓተ ጾታ ክበብ የስብሰባ ሂደት

- ክበቡ ስብሰባ በሚያካሄድበት ወቅት አባላት ውይይታቸውን በነጻነት እንዲያካሂዱ ለማድረግ የስብሰባ ቦታዉ ፀጥታ የሰፈነበት አካባቢ ወይም ክፍል ውስጥ መሆን አለበት።
- በክበቡ በኩል አሳሳቢ የሆኑ ጉዳዮች በሚያጋጥሙበት ወቅት የውይይት ቦታው ወይም ክፍሉ ምስጥራዊ እና ገለልተኛ እንዲሆን በማድረግ ሌሎች አካላት በተለያየ መልኩ የማወክ ችግር እንዳይፈጥሩ መደረግ አለበት። ስለሆነም የውይይት ቦታን በተቻለ መጠን ከመማሪያ ክፍል የተለየ እና የተሻለ ማድረግ ያስፈልጋል።
- በክበቡ በኩል የሚካሄድማንኛዉም ስብሰባ ሆነ ስልጠናጊዜዉና ቦታዉ በአባላት ስምምነት መሰረት መወሰን ይኖርበታል።እያንዳንዱ የክበቡ ወይም ንኡስ ክበቡ አባላት ይሁንታ የሰጡበት ቦታ እና ሰዓት ሆኖ ይሄው ውሳኔ ለትምህርት ቤቱ አመራር እና ለተሳታፊዎች ቤተሰብ መገለጽ አለበት።

የስብሰባ እና ውይይት ሰዓቶች ፡ በእረፍት ሰዓት እና በተቃራኒ ፈረቃ (ከመደበኛ የትምህርት ሰዓት ውጭ) መሆን አለበት። የክበቡ ውይይቶች የመማር ማስተማር ሂደትን የሚያቀላጥፍ እና የሚረዳ ስለሆነ የትምህርት ቤት አመራር እና መምህራኖች ይሄንኑ በውል ተገንዝበው በክበብ በኩል የሚካሄዱ ውይይቶች እና ስልጠናዎችን መደገፍ እና ማበረታታት ይኖርባቸዋል።

የውይይት ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ ከ 60 ደቂቃ በላይ ማለፍ የለበትም። የውይይቱ ጊዜ በሳምንት ከሁለት ቀን በላይ መሆን የለበትም።በተገዳኝ ትምህርት በኩል የሚሰጠው የህይዎት ክህሎት

በስርዓተ ጾታ ክበብ የውይይት ጊዜ የአባላት እኩል ተሳትፎን ማጎልበቻ መንገዶች

- ዉይይት በሚካሄድበት ወቅት ሴቶችና ወንዶች እኩል የመሳተፍ ዕድል እንዲኖራቸው ሀሳብ እንዲሰጡ ማበረታታት እና ማገዝ
- የመናገር ድፍረት ለሌላቸው እና ሀፍረት ለሚሰማቸው ሴት እና ወንድ ተማሪዎችን በመለየት ተጨማሪ እገዛ በማድረግ ሀሳብ እንዲሰጡ ለማበረታታት ፤ ለምሳሌ በቃል “ንበገዝ ነሽ/ህ” ፣ “ጥሩ ሀሳብ ነው” ወዘተ ማለት
- የውይይት ተሳታፊዎች ለሚሰጡት ሀሳብ ሌሎች ጓደኞቻቸው እንዳያሽሟጥጡባቸው ዕድል አለመስጠት፡

ስልጠና ዓመታዊ የትምህርት ጊዜን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሆኖ ከመደበኛ የክፍል ጊዜ ጋር በማይጋጭ መልኩ መሰጠት ያለበት ሲሆን የሚወስደዉ ጊዜ እንደ ስልጠናዉ ይዘት የሚወሰን ይሆናል።

ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስብሰባ

የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ስብሰባ ወር በገባ በመጀመሪያ ሳምንት የሚካሄድ ይሆናል። የስብሰባው አጀንዳም የክበቡን ወርሃዊ የስራ እንቅስቃሴ በመገምገም መስተካከል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠት ነው።

3.4. የሥርዓተ ፆታ ክበብ ዋናዋና ተግባራት

የሥርዓተ ፆታ ክበብ የሚቋቋምበት ዋና አላማ በክፍል ውስጥ የሚተገበረውን ስርአተ ትምህርት በተጓዳኝ በሚከናወኑ ተግባራት እና የክህሎት ስልጠናዎን በመስጠት የፆታ እኩልነትን ለማስፈን ጥረት ማጎልበት ነዉ።

የክበቡ ዋና ዋና ተግባራት የጾታ እኩልነትን ጠቀሜታ እና አስፈላጊነትን ማስተዋወቅ፣ ለሴት እና ወንድ ተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦትቶችን ማሟላት፣ የሰብአዊ መብቶችን በተለይም የህጻናት መብቶችን ማስጠበቅ፣ በሴት ተማሪዎች ትምህርት ላይ የሚስተዋሉ መሰናክሎች ማስወገድ፤ ድርብ ችግር ያለባቸዉ አካል ጉዳተኛ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች ላይ የሚታዩ ችግር መቅረፍ የሚሉ ናቸዉ።

እነርሱም: -

- የህይወት ክህሎት ስልጠና መስጠት፤
- በጾታ እኩልነት ላይ የማህበረሰብንቅናቄ እና ግንዛቤ ማሳደጊያ ስራዎችን ማካሄድ፤
- የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ ላይ ትምህርት እና አገልግሎት መስጠት፤
- ጾታዊ ጥቃት ሰለባ ሆኑ ሴት እና ወንድተማሪዎች በመለየት መለስተኛ የምክር አገልግሎት መስጠት፤
- በጾታ እኩልነት ላይ ከባለድርሻዎች እና የልማት አጋሮች ጋር ተቀናጅቶ መስራት፤
- ሴት እና ወንድ ተማሪዎች እኩል ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራዊ የምርምር እና ጥናት ስራዎችን ማካሄድ።

3.4.1. የህይወት ክህሎት ስልጠና መስጠት

በክፍል ውስጥ በሚሰጠው ትምህርት ከሚጨበጠው እውቀት እና ክህሎቶች በተጨማሪ የተለያዩ መሰረታዊ እና ተሸጋጋሪ የሆኑ ክህሎቶች ማዳበርያስፈልጋል። እነዚህ የህይዎት ክህሎት ስልጠናዎች ሴት እና ወንድ ተማሪዎች በትምህርታቸው ወጤታማ እንዲሆኑ በማድረግ የወደፊት ራዕይ ያላቸው እና በዕለት ከዕለት ህይወታቸው የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች የሚቋቋሙ፤በግል እና በቡድን ብቁ እና ንቁ የሆኑ ዜጎች ለማድረግያግዛቸዋል። ክበቡ በሥርዓተ ፆታ ላይ ያሉ ግምቶች፣ ሚናዎች እና ልማዶች ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ መረጃን፣ እውቀትን እና ክህሎትን ለመለዋወጥ ዕድል ይሰጣል።

ተማሪዎች በዕለት ከዕለት ኑሮቸው የህይወት ክህሎቶች ኢ-መደበኛ በሆነ እና ባጋጣሚ ሊያገኙዋቸው ይችላሉ። ሆኖም ግን መደበኛ ያልሆነ ወይም በተጓዳኝ ትምህርት ውስጥ የሚያገኟቸው ከሆነ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል።

- ግልፅ ግቦች ያላቸዉ፣
- በእድሜ እና በጾታ የተለዩ ፣

- መደበኛ ግን ተለማጭ የሆኑ፣
- አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ፣
- በጊዜ የተገደቡ፣
- አሳታፊ እና ጨዋታን መሰረት ያደረገ፣
- አካታች እና የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች ፍላጎቶች ያገናዘበ (የምልክት ቋንቋ፣ ብሬይል፣ ለእንቅስቃሴ አመቺ መሰረተ ልማት፣ ወዘተ) ሲሆኑ የተሰጠዉን ስልጠና ውጤቶች በመገምገም እና የተደረሰበት ደረጃ መታወቅ ይኖርበታል።

የስርዓተ ጾታ ክበበባት እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ከተለያዩ ሀገራት የተገኙ ተሞክሮዎች

ኬንያ-ኤ.ቪ.ኤፍ. ፒ.

- የክበቡ አባላት አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ቡድኖች ይከፋፈላሉ፤፤
- ውይይቶች በሴት ተማሪዎች ችግሮች ላይ የተመሰረቱ ናቸው።
- ችግሮችን ለመፍታት በሚካሄዱ ውይይቶች ተሳታፊዎች ሀሳባቸው እንዲያቀርብ ይደረጋል።
- በውይይት ወቅት አባላት በመሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች መርሀዎች ላይ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ይደረጋል።
- አባላት በውይይታቸው ወቅት ለተማሪዎች በተለይም ለሴት ተማሪዎች አደገኛ የሚባሉ አካባቢዎችን የመለየት ስራ ይካሄዳል።

ህንድ- ዲ. ህን

- የክበቡ አባላት ከጤና ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት ይሰራሉ።
- የደም ማነስ ህመም ያለባቸውን ልጆች ይለያሉ።
- ክበቡ ለሴት ተማሪዎች ቤተሰብ በደም ማነስ መንስዔዎች እና መከላከያ ዘዴዎች ላይ ትምህርት ይሰጣሉ።
- ክበቡ በስርዓተ- ምግብ እና በብረት ማዕድን አወሳሰድ ላይ የምክር አገልግሎት ይሰጣል።

Source: “A Practical Handbook for Creating and Leading a Girls’ Club.”*WomenStrong International.* 2018

-

3.4.2፡.በጾታ እኩልነት ላይ የህብረተሰብ ንቅናቄ ስራዎችን ማካሄድ

የሥርዓተ ፆታ ክበባት ትምህርት ቤቶችንና የአካባቢ ማህበረሰብ በማስተባበር በስርዓተ ጾታ ላይ የሚንጸባረቁ አዎንታዊ ልማዶች እንዲበረታቱ፣ ባንዛሩ ደግሞ አሉታዊ የሆኑ ልማዶች እንዲወገዱ ይሰራሉ። ክበባቱ አለማቀፋዊ፣ ሀገራዊና አካባቢያዊ ጭብጦችንና በዓላትን በመጠቀም ህብረተሰቡን ተሸጋሪ የሆኑ የሥርዓተ ጾታ ለውጦች እና አስተሳሰቦችን እንዲመርጡ ይሰራሉ።

የስርዓተ ጾታ ክበባት ከትምህርት ቤቱ አመራር ጋር በመቀናጀት የተለያዩ በዓላትን በመጠቀም የንቅናቄ ስራዎችን ያካሂዳሉ። በዚህ መሰረት ዓለምአቀፍ የልጃገረዶች ቀን፣የነጭ ሪቫን ቀን፣ ማርች ስምንት የሴቶች ቀን ፤የአካል ጉዳተኞች ቀን፣ የሰብአዊ መብቶች ቀን፣ የፀረ ኤች.

አይ. ቪ/ ኤድስ ቀን ፣የሴት ልጅ ግርዛት ተቃውሞ ቀን፣ በትምህርት ቤቶች የወላጆች ቀን ወዘተ በመጠቀም የተለያዩ የንቅናቄ መርሃ-ግብሮችን ያካሂዳሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት በዓላት በተጨማሪ የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን በትምህርት ቤት እና በማህበረሰቡ ለማስተዋወቅ ሌሎች አካባቢያዊና፣ ህዝባዊ በዓላትን መጠቀም ይቻላል።

3.4.3.የወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ ላይ ትምህርት እና አገልግሎት መስጠት

የሴት ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታን ማገዝ

እንደሚታወቀዉ አንድ ሴት በወር ውስጥ የወር አበባ በማየት ከሶስት እስከ አምስት ቀን ትቀያለች። ይህ የወር አበባ የቆይታ ጊዜ በዓመት ሲሰላ ከ 30 እስከ 50 የትምህርት ቀናት ይደርሳል ። አንዳንድ ሴት ተማሪዎች ላይ የወር አበባ ከፍተኛ የህመም ስሜት ስለሚያስከትል ከትምህርት ቤት የሚቀሩበት ሁኔታ ይፈጠራል ። በመሆኑም በዓመት ውስጥ አንድ ወር ከ 20 ቀን ትምህርት የማ ቋረጥ ዕድል ሊያጋጥማቸው ይችላል ።

ከስርዓተ ጾታ ክበብ ዓላማዎች መካከል አንዱበአፍላ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ኮረዳ ሴት ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታ ጊዜያቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሸራረፍ በሚጠበቀው ልክ እንዲገዝ ማድረግ ነው። ስለሆነም በወር አበባ ምክንያት ሴት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ለተወሰኑ ቀናት በሚቀሩበት ወቅት የክበቡ አስተባባሪዎች እና አባላት ወደ ቤት በመሄድ በመጠየቅ መወሰድ ያለባቸዉ ድጋፎችን ማከናወን ይኖርባቸዋል።

በተለይ ሴት ተማሪዎች በወር አበባ ምክንያት ወይም ባልተፈለገ እርግዝና ከትምህርት ቤት የሚቀሩ ከሆነ የሚያስፈልገውን ምክር እና አገልግሎት በመስጠት ወደ ትምህርት እንዲመለሱ ማድረግ አለባቸው።

ይሄንም ሲያደርጉ እንደዚህ ዓይነት ያጋጠማቸው ሴት ተማሪዎች ለትምህርታቸው ቅድሚያ መስጠት እና የወደፊት ብሩህ ዕድላቸው ከትምህርት ጋር የተቆራኘ ስለመሆኑ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል።

ሴት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ እያሉ የወር አበባ ሲታያቸው የነበረውን መገለል እና መሸማቀቅ በማስወገድ ላይ የስርዓተ ጾታ ክበባት አመርቂተግባራትን ስፈጽሙ የኖሩ ሲሆን አሁንም በመፈጸም ላይ ናቸው። ይህ ተግባር አሁንም ክበባቱ ከትምህርት ቤቱ አመራር ጋር በመመካከር **ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። ለተግባራዊነቱም ለዚህአገልግሎት የሚዉል ፀጥታ የሰፈነበት ክፍል ለአገልግሎቱ የሚዉሉቁሳቁሶችን በማማለት ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ይህ ክፍል ሴት ተማሪዎች የወር አበባ በሚያዩበት ጊዜ የሞይስ መቀየሪያ እና እረፍት ለማድረግ እንዲሁምለንብብ አገልግሎት የሚውል ይሆናል።ከዚህ በተጨማሪ የወር አበባን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ-ግብሮችን ለወንድና ሴት ተማሪዎች ተጠናክረዉ የሚቀጥሉ ይሆናል።**

3.4.4. የጾታዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት መለስተኛ የምክር አገልግሎት መስጠት

የሥርዓተ ፆታ ክበባት በጾታዊ ጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴት እና ወንድ ተማሪዎችንበመለየት መለስተኛ የምክር አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ሆኖም ግን በትምህርት ቤት ደረጃ የሚሰጠው መለስተኛ የምክር አገልግሎት ተጎጂዎቹ በመስኩ በሰለጠኑ ባለሙያዎች (በማህበራዊ ሳይንስ የሰለጠኑ ወይም ስነልቦና ሳይንስ የተማሩ ባለሙያዎች ወዘተ) አማካኝነት ጥልቅ ድጋፍ እስኪያገኙ ድረስ ብቻ መሆን እንዳለበት ሊታወቅ ይገባል። እነዚህ ባለሙያዎች ክበቡ እና የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከሌሎች መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቀማት ጋር በሚያደርጉት የስራ ግንኙነት የሚመቻች ይሆናል። ይህ አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት ተጎጂውን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት።

3.4.5. ከባለ ድርሻዎች እና የልማት አጋሮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር መንቀሳቀስ

የሥርዓተ ፆታ ክበባት ለክበቡ አባላት የሚሰጠውን አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በትምህርት ቤት ውስጥ እና ውጭ ከሚገኙ ባለድርሻዎች እናየልማት አጋሮች ጋር ግንኙነት መፍጠር አለባቸው።

3.4.5.1. የውስጥ ባለድርሻ አከላት

የውስጥ ባለድርሻ አካላት በትምህርት ቤቱ የሚገኙ ሌሎች ክበባትን፣ ዲፓርትመንቶችን፣ ለተለያዩ የትምህርት ተግባራት በትምህርት ቤቱ በመቋቋም የሚንቀሳቀሱ ኮሚቴዎችን ያካትታል። ሚኒ ሚዲያ እና ሌሎች ክበባት የተዛቡ የሥርዓተ ጾታ ግንኙነቶች እና መስተጋብሮች ላይ ያለውን ችግር ከመቅረፍ አኳያ፣የሴትእና ወንድ ተማሪዎች አቅም ለመገንባት የሚረዱ መልዕክቶችን በማስተላለፍእናመረጃዎችን በመስጠትየባህሪ ለውጥ ለማምጣት የሚረዱ ጠቃሚ መድረኮች በመሆናቸዉ እንደ የውስጥ ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተዉ መስራት ይኖርባቸዋል።

በተጨማሪም በትምህርት ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ አደረጃጀቶች እና መድረኮች፤ለምሳሌ የመምህራን ማህበር፣ የወላጅ መምህር ተማሪ ህብረት፣የትምህርትዓይነቶች ለማስተባበርየተቋቋሙ ዲፓርትመንቶች እንዲሁም የትምህርት ቤቱ አመራርና አስተዳደር መደበኛ ስብሰባዎች በሚካሄዱበት ወቅት የክበቡን አጀንዳዎች በመያዝ፣ተቀናጅተዉ መስራት ይኖርባቸዋል።

ክበባት በሥርዓተ ትምህርቱ የተቀመጠውን ተፈላጊ የመማር ውጤት እና ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረገ የአመራር ክህሎት ልምምድ ላይ ክፍተት ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት ድጋፍ ለማድረግ "ሥርዓተ ፆታ ምላሽ አሰጣጥየማስተማር ዘዴ" ተግባራዊበማድረግ በክፍል ውስጥ በሚካሄደዉ የመማር ማስተማር ሂደት ከስርዓተ ጾታ አንጻር በመቃኘት ሁለቱም ጾታዎች እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ ተቀናጅቶ መስራት አስፈላጊ እና ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል።

በተጨማሪም ክበባቱ የትምህርት ቤቱ አመራር እና ሌሎች የትምህርት ቤቱ አደረጃጀቶች ሀብት በማፈላለግ (የቴክኒክ፣ የገንዘብ እና የቁሳቁስ) ተጋላጭ ለሆኑ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች አካል ጉዳተኞች እና ልዩ ፍላጎት ለሚሹ ተማሪዎችበተለይም ሴቶችንተደራሽ ለማድረግ መስራት ይኖርባቸዋል።

3.4.5.2. የውጭ ባለድርሻ አካላት

መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በጎ አድራጊዎች፣ የግል ባለሀብቶች፤ ታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ በስርዓተ ጾታ እኩልነት ላይ ስልጠና በመስጠት፣ ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ (ለምሳሌ የህግ አገልግሎት፣የጤና እንክብካቤ /አገልግሎት) መስጠት፣ሀብትን በማፈላለግ ተግባር ወዘተ የስርዓተ ጾታ ክበብ ተግባራትን መደገፍ ይኖርባቸዋል።

የጾታዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሴት እና ወንድ ተማሪዎችንበመለየት መለስተኛ የምክር አገልግሎት ለማሰጠት የሚመለከታቸዉ አካላት መነተል ያለባቸዉ መሰረታዊ መርሆች

በአርዓያነት/ተምሳሌት / የሆኑ ግለሰቦች ስራ ማስተዋወቅ

ለክበቡ መሰብሰቢያ ቦታ በማዘጋጀት፣ የሜንተሪንግ አገልግሎት በመስጠት እና የተለያዩ ዕድሎችን በማስፋትመምህራን እና ርዕሳነ መምህራን ክበቡን በግንባር ቀደም ደጋፊ መሆን ይኖርባቸዋል።በትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ አደረጃጀቶች መካከል ከሚጠበቀዉ ቅንጅታዊ አሰራር በተጨማሪ በየደረጃዉ በሚገኙ የትምህርት ተቋማት መካከል በሚፈጠር ቅንጅታዊ አሰራር የክበባትን እንቅስቃሴ ማገልበት የሚጠበቅ ይሆናል።

የወጣት ተምሳሌቶችን ስራ ማስተዋወቅ፤-የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃትምህርት ቤቶች በአካባቢያቸዉ ከሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወይም ሌሎች የትምህርት ተቋማት ጋር የቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር ወጣት ተምሳሌት የሆኑ/በአርዓያነታቸዉ የሚታወቁ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች ልምዳቸዉን እንዲያካፍሉ በማድረግ ተቀናጅቶ መስራት ይቻላል።

ለምሳሌ በሳይንስ እና ሂሳብ ትምህርቶች በአርዓያነት/በተምሳሌትነት የሚታወቁትን ወደ ትምህርት ቤት በመጋበዝ ለክበቡ አባላት ተሞክሮአቸዉን እንዲያካፍሉ ማድረግያስፈልጋል።

በተመሳሳይ የትምህርት ተቋማት እና በሌሎች የጥናት ዘርፎች ለምሳሌ በንግድ ፤በሙዚቃ እና በሌሎች የስነ ጥበብ ዘርፎች ዝነኛ እና ስኬታማ የሆኑ ወጣት (ሴት እና ወንድ) ተማሪዎችን በመጋበዝ ለክበቡ አባላት ልምዳቸውን በማካፍል ተሰጥኦ ያላቸውን የክበብ አባላት እንዲያነሳሱ ማድረግ፤-

በመንግስት እና በተለያዩ በንግድ እና በመሳሰሉት ድርጅቶች የተሰማሩ ልዩ ፍላጎት የሚሹ /አካል ጉዳተኞች ወጣቶችበትምህርት ቤት ለሚገኙ ልዩ ፍላጎት ለሚሹ እና አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች ልምዳቸውን በማካፈል አነርሱም የወደፊት ዓላማቸዉን ለማሳካት ምን ማድረግ እንዳለባቸዉ ከወድሁ እንዲዘጋጁ ማድረግ፤-

በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ አደረጃጀቶች እና ሌሎች እንቅስቃሴዎችን መጠቀም

የትምህርት ቤት ሚኒ ሚዲያ መጠቀም፤- በሰንደቅ አላማ ስነ ስርዓት ላይ፤ በዕረፍት እና የፈረቃ ለዉጥ በሚደረግበት ሰዓትተማሪዎች በጾታ እኩልነት፣ብወርአበባ ንጽህና አጠባበቅ፤

3.4.6. የሴት እና የወንድ ተማሪዎች እኩል ተጠቃሚነት ምርምር እና ጥናት ማካሄድ

የሥርዓተ ፆታ ክበባት ሴትና ወንድ ተማሪዎች ከተግባራዊ ጥናትና ምርምር ጋር የተያያዙ ዕድሜቸዉ በሚፈቅደዉ ልክ እውቀት፣ክህሎት እና ችሎታ በሚጠይቁ ተግባራት ላይ የመሳተፍ እድል እንዲያገኙ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ተግባራዊ ጥናትና ምርምሮች መረጃን መሰረት ያደረገ የሥርዓተ ፆታ ክበባት እቅድ እና ትግበራን ከመደገፍ ባሻገር ሴት እና ወንድ ተማሪዎች የግል አስተያየቶችና አመክንዮቶችእውነትን መሰረት ያደረጉ መሆን እንዳለባቸዉ ከትምህርት ቤት ጀምሮ እንዲያዉቁ ከማድረግ ባሻገር ምክንያታዊነትን የህይወት መመሪያቸዉ አድርገዉ እንዲወስዱ ይረዳቸዋል።

ጥናትና ምርምር የሚካሄድባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ገደብ ባይበጅላቸውምየሚከተሉትን ጭብጦች የሚያካትቱ ይሆናል።

- በትምህርት ቤት ፆታ እና አካል ጉዳተኝነትን መሰረት ያደረጉ አግላይና ነገሮች መለየት፤
- በትምህርት አይነት (ለምሳሌ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና፣ በሂሳብ) በጾታ የተለዩ የመማር ውጤቶች፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ልማዶች በሴቶች እና ወንዶች ወደ ትምህርት መምጣት፣ በትምህርት ቤት መቆየት እና ማጠናቀቅ ላይ ያላቸዉ አሉታዊ ተፅእኖዎች፤
- በተጓዳኝነት የሚሰጠው የህይወት ክህሎት ትምህርት አሰጣጥ ሂደት እና ያስገኘዉ ዉጤት፤
- በትምህርት ቤት ዉስጥለሴት እና ወንድ ተማሪዎች ተደራሽ የሆኑ አገልግሎቶች (ለምሳሌ ዉሃ እና የጽዳት አቅርቦት (WASH)፣ የጤና፤ ቱቶሪያል እና የምክር አገልግሎት፣፣ የግቢ አጥር መኖር፣ጾታን መሰረት ካደረገ ጥቃት እና ከሱስ የፀዳ ትምህርት ቤት እና አካባቢወዘተ) ላይ የተገኙ ለዉጦች፤፣

ህጻናት የግል ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ለማድረግ በተግባራዊ ምርምርእና ጥናት ሥራ እንዲሳተፉ ማድረግው ወሳኝ ነው። ወጣት ሴቶች እና ወንዶች ስለግል ሁኔታቸው መረጃ ለመስጠት ተመራጭ ናቸው።

ሁሉም ወጣት ወንዶች እና ሴቶች ራሳቸውን የተመለከቱ ሀሳቦች እንዲከበሩላቸው ለማድረግ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (1989) ባወጣዉየህጻናት መብቶችድንጋጌ ላይ ተመልክቷል።ሴት እና ወንድ ወጣቶች የለውጥ ተዋናይ መሆን እንደሚችሉ ልብ ሊባል ይገባል። እንደማናችንም ሃሳባቸው የሚመሰረተው ከበፊት ልምዳቸው በመነሳት መሆኑ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል። የተግባራዊ ጥናትእና ምርምር ውጤት ግኝቶች ተዓማኒነት፣ ትክክለኛነት እና አካታችነት መለኪያው የህጻናቱ ተሳትፎ መሆኑ የሥርዓተ ፆታ ክበባትማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።



ክፍል አራት

የሥርዓተ ጾታ ክበብ ክትትል፣ ድጋፍ እና ግምገማ

የሥርዓተ ጾታ ክበብ እንቅስቃሴን በመደገፍ የማጠናከር ስራ የእለት ተዕለት ተግባር ሆኖ የሚቀጥል ሲሆን በሚታዩ ችግሮች ላይ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የተወሰነ ወቅት ወስዶ ክትትል እናግምገማ ሥራማካሄድን ይጠይቃል። በዚህ መሰረት የክትትል እና

ግምገማስራ በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያእና መጨረሻ ወራቶች ቼክሊስት(የሚታዩ ጉዳዮችን የሚያሳይ የስራ መዘርዝር) በማዘጋጀት እና የክትትል እና ግምገማ ስራዉን በተያዘለት ጊዜ ማከናወን ያስፈልጋል።

4.1. በሥርዓተ ጾታ ክበብ ክትትል እና ድጋፍ ስራ የሚሳተፉ አካላት

የክትትል እና ግምገማ ተግባራት በትምህርት ቤቱ አስተዳደር እና በመምህራን መከናወን ይኖርበታል። በተጨማሪም የትምህርት ቤት የክላስተር ሱፐርቫይዘሮች በየትምህርት ቤቶች የሚገኙ ክበባትን በቋሚነት የሚከታተሉበት ሁኔታ እንዳለ ሁሉ የሥርዓተ ጾታ ክበባትንም መከታተል፤ ድጋፍ መስጠት እና ግማገማ የማካሄድ ሃላፊነት ይኖርባቸዋል። የክልልና የፌዴራል የዘርፉ ባለሙያዎች የመመሪያውን አተገባበር አስመልክቶ የክትትልናግምገማ ተግባር ሊያከናውኑ ይችላሉ። መመሪያውን ማሻሻል ካስፈለገ የሚመለከታቸውየክልልና የፌዴራል አካላት ግምገማ በማካሄድ ሊያሻሽሉት ይችላሉ።

4.2. የሥርዓተ ጾታ ክበብ ተግባራት የክትትል፣ ድጋፍ እና ግምገማ ርዕሰ ጉዳዮች

ከላይ የተጠቀሱት ባለድርሻ አካላትን ጨምሮ ሌሎች በትምህርት ዘርፉ ድርሻ ያላቸው በትምህርት ቤት ደረጃ የተቋቋሙ የሥርዓተ ጾታ ክበባት እንቅስቃሴ የክትትል እና ድጋፍ ስራ በሚያከናውኑበት ወቅት ትኩረት ማድረግ ካሉባቸዉጉዳዮች መካከልከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዋናዋናዎቹ ሲሆኑ፤ እነዚህ ባለድርሻዎች ወደ ሥራዉ ከመግባታቸዉ በፊት ግልፅ የሆነ ቼክሊስት በማዘጋጀት ክትትል፤ ድጋፍ እና ግምገማ በማካሄድ የተገኙ ውጤቶችን በመተንተን ወድያዉኑ ለትምህርት ቤቱና የስርዓተ ጾታ ክበብ ሪፖርቱን ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

- የክበቡ አደረጃጀት እና አመራር በመመሪያው መሰረት መከናወኑ፤
- የክበቡ ዋናዋና ተግባራት አፈጻጸም፤
- በክበቡ እንቅስቃሴ የተገኙ ውጤቶች፣ ተግዳሮቶች እና መልካም ተሞክሮዎች፤
- በክበቡ አጠቃላይ እንቅስቃሴ እና የተገኙ ዉጤት እና መዘግቦ የማስቀመጥ ተግባር ፤

4.3. የስርዓተ ጾታ ክበብ የዉጤት ደረጃዎች፤ሂደት፤አመልካች እና ሥልቶች

የሂደት አመልካቾች	መረጃ ማግኛ ዘዴዎች	ስልቶች
የክፍል ውስጥ ትምህርት አቀራረብ ሂደት የአካታችነት ስነ ትምህርት ትግበራን በመከተል ለሴት እና ወንድ ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ ማድረግ ያለዉ አስተዋጽኦ	የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ለሴት ተማሪዎች ቃለ መጠይቅ ማድረግ	ቼክሊስት
በህጻናት መብቶች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የወሰዱ ሴት እና የወንድ ተማሪዎች በጾታ	የስርዓተ ጾታ ክበብ መዛግብት እና ሪፖርት	አቴንዳንስ በመያዝ
የወር አበባ ለሚታያቸው ሴት ተማሪዎች የድርሻቸዉን ለመወጣት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ላይ የተሳተፉ አፍላ ወንድ ተማሪዎች በመቶኛ	የስርዓተ ጾታ ክበብ መዛግብት እና ሪፖርት	አቴንዳንስ በመያዝ
የህፃዎት ክህሎት ላይ መረጃ እና ዕውቀትለማስጨበጫ በተያዘዉ ክፍለ ጊዜ የተሳተፉ ኮረዳ ሴት ተማሪዎች በመቶኛ	የስርዓተ ጾታ ክበብ መዛግብት እና ሪፖርት	አቴንዳንስ በመያዝ
ከስርዓተ ጾታ ጉዳዮችን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ በትምህርት ቤት ፋሲሊቲ ላይ የተከናወነ ትንተና	የሥርዓተ ጾታ ጉዳዮችን ተደራሽ ማድረግ ላይ የተካሄደ ትንተና ውጤት	አሳታፊ የተግባር ጥናት
የመካከለኛ ውጤት አመልካቾች	መረጃ ማግኛ ዘዴዎች	ስልቶች
በህጻናት መብቶች ማክበር ላይ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ግንዛቤቸዉ ያደገ ሴት እና ወንድ ተማሪዎች ቁጥር በመቶኛ	የህጻናት መብት ለማሳወቅ የወጣ መርሃ-ግብር ትግበራ ሂደት	ቃለመጠይቅ፤ የቡድን ውይይት፤ መጠይቅ

4.4 የስርዓተ ጾታ ክበብ መረጃን ማጠናቀር

መረጃን አጠናቅሮ መያዝ የክበቡን ተግባር እና ውጤቶችን ለመለካት ብሎም መሻሻል የሚገባቸውን ለመለየት ያግዛል።

የስርዓተ ጾታ ክበብ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና አባላት በተሰጣቸዉ ተግባር እና ኃላፊነት መሰረት በክበቡ የሚከናወኑ ተግባራትን መዝግቦ በመያዝ ለክበቡ አባላት እና ለሌሎች አካላት ስለ ክበቡ እንቅስቃሴ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም መልካም ተሞክሮዎች፥ ሊሻሻሉ ስለሚገባቸው ነገሮች እና በሴት እና ወንድ ተማሪዎች ህይወት ላይ ያለውን ለውጥ ለማጤን ያግዛል።

ባለድርሻዎች እና የአካባቢው ማህበረሰብ አባላት ስለ ክበቡ ማወቅ በሚፈልጉበት ወቅት በቀላሉ መረጃ ለመስጠት እንዲያግዝ መረጃን መዝግቦ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። ሆኖም ግን የሚጠናቀረው መረጃ ውስብስብ ሳይሆን የክበቡ አባላት የሆኑት ተማሪዎች (ሴት እና ወንድ) ዝርዝር በአንድ መዝገብ የሚያዝ ሆኖ ሙሉ ስም፥ ጾታ፥ የክፍል ደረጃ፤ ዕድሜ ፤አባል የሆነችበት/በት ቀን እና ስለ አባሏ/ሉ እንደ የአስፈላጊነቱ ተጨማሪ መረጃ መያዝ ያጠቃልላል። ሌሎች መረጃዎች ለምሳሌ አቴንዳንስ፤ የክፍል ደረጃ ወዘተ በክበቡ የስራ ዘመን ሊሰበሰቡ ይችላሉ።

በክበቡ ውስጥ አፍላ ሴት ተማሪዎች ስለ ስነ ተዋልዶ ጤና በዝርዝር ዕውቀት የሚያገኙበት መድረክ እንደመሆኑ መጠን ስለ የወር አበባ ዑደት እና ተያያዥ ሁኔታዎችን የሚያመለክት መረጃ መዝግቦ መያዝ ጠቃሚ ይሆናል። ይህን በማድረግ አፍላ ሴት ተማሪዎች ስለ ራሳቸው ስነ ተዋልዶ ጤና የበለጠ ግንዛቤ እንዲያገኙ ከማድረግ አልፎ የስርዓተ ጾታ አስተባባሪ እና ሌሎች የክበቡ አመራሮች ሴት ተማሪዎች በወር አበባ ምክንያት ከትምህርት ቤት እንዳይቀሩ እና አስፈልጊውን እገዛ ለማድረግ እንዲችሉ ጥሩ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል።

